**የኮሌጅ በአል ክውነቶች በኤፕረልና ሜይ እየተቃረቡ ነው።**

እነዚህን ለኮሌጅ የሚያዘጋጁቸውን የኢፕረልና የሜይ ሶስት ድርጊቶች የMCPS ተማሪዎችና ወላጆች እንዲከታተሉ እናበረታታለን።

**አመታዊው የMontgomery County ብሄራዊ የኮሌጅ በአል ሮብ፣ ኤፕረል 9፣ እና ሀሙስ፣ ኤፕረል 10 በAgricultural Center, 16 Chestnut St. in Gaithersburg** ይከናወናል። ይህ ነፃ ድርጊት በደርዘኖች የሚቆጠሩ የኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች ተወካዮች ያቀርባል፣ እናም ለተማሪዎችና ለወላጆቻቸው የኮሌጅ መግቢያዎች ሂደት መገልገያዎችን ያቀርባሉ። በአሉ በሁለቱም ቀኖች ከ9:45 a.m. – 12:30 p.m. ይከናወናል እንዲሁም ሮብ እለት ከ6:30 – 8:30 p.m. ይከናወናል። በአሉ ነፃ ነው ከ8-12 ክፍል ለሚገኙ ተማሪዎችና ወላጆቻቸውም ክፍት ነው። ተጨማሪ መረጃ.

**የኮሌጅ ዝግጅትና ስኮላርሺፕ በአል ቅዳሜ፣ ሜይ 10 ከ1-4 p.m.** በሼዲ ግሩቭ ዩኒቨርሲቲዎች 9630 Gudelsky Dr. in Rockville ይከናወናል። በአሉ ኢላማ የሚያደርገው ከ6ኛ እስከ 10ኛ ክፍል የሚገኙ ተማሪዎችንና ወላጆቻቸውን ነው። ተሳታፊዎች ከኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች ተወካዮችን ለማግኘት እድል ይኖራቸዋል፣ እናም የተለያዩ አሰሪዎች ተገኝተው ግንዛቤ ይሰጣሉ ለጥያቄዎችም መልስ ይሰጣሉ። በበርካታ ርእሶች ዎርክሾፖች ይኖራል፣ እንዲሁም ስለ ፋይናንሳዊ እርዳታና የስኮላርሺፕ እድሎች መረጃዎች ይኖራሉ። ተመሪዎችና ቤተሰቦች የUSG (የሼዲ ግሩቭ ዩኒቨርሲቲዎች) ካምፐስ ተዛውረው ለማየት በተጨማሪ እድል ይኖራቸዋል። የቦታ ጥበት ስላለ፣ መመዝገብ ያስፈልጋል። በMCPS Parent Academy (የወላጅ አካዴሚ) ድር ጣብያ መመዝገብ ይቻላል ወይም ወደ 301-279-3100 ይደውሉ

**ACT ወይስ SAT? የተሻለውን የፈተና አይነት ለልጅዎ እንዴት እንደሚመርጡ**
**ሀሙስ፣ ሜይ 15፣** የMCPS የወላጅ አካዴሚ በሁለቱ የኮሌጅ መግቢያ ፈተናዎች መካከል ያለውን ልዩነት በሚመለከት ለወላጆች ዎርክሾፕ ያካሂዳል። በዚህ ክፍለ ጊዜ፣ ወላጆች ለልጃቸው የትህምርት ዘይቤና ማንነት የትኛው ይበልጥ እንደሚስማማ ለመወስን

እንዲያግዛቸው ከሁለቱ ፈተናዎች ናሙና ጥያቄዎች የያዘ የ60 ሴኮንድ ግምገማ የመውሰድ እድል ይኖራቸዋል። ዎርክሾፑ ከ7 – 8:30 p.m. የሚከናወን ሆኖ ቦታውም በWalter Johnson High School, 6400 Rock Spring Drive in Bethesda ነው።

[የወላጅ አካዴሚ]

**የሰመር ት/ቤት ምዝገባ ኤፕረል 3 ይጀምራል**

ለ2014 የ2ኛ ደረጃ ት/ቤትና የኤሌሜንታሪ ሰመር ት/ቤት ፕሮግራሞች ምዝገባ ሀሙስ፣ ኤፕረል 3 ይጀምራል።

ለ2ኛ ደረጃ ት/ቤት ፕሮግራሞች፣ ተማሪዎች በት/ቤታቸው መደበኛ አማካሪ በኩል መመዝገብ አለባቸው። ፕሮግራሞቹ አራት ቦታዎች ላይ ይቀርባሉ፡- Montgomery Blair፣ Paint Branch፣ Watkins Mill እና Thomas S. Wootton 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች። የመጀመርያው ክፍለ ግዜ ጁን 23 - ጁላይ 11 ሲሆን፤ ሁለተኛው የሚከናወነው ከጁላይ 15 - ኦገስት 1 ነው። ምዝገባው ለክፍለ ጊዜ 1 ጁን 9 ያልቃል ለ2ኛ ክፍለ ጊዜ ደሞ ጁን 25 ያልቃል። **የዘገየ ምዝገባ ተቀባይነት የለውም** ስለ ምዝገባ ሂደት ተጨማሪ መረጃ [የ2ኛ ደረጃ ሰመር ት/ቤት ድር ጣብያ ጎብኙ]።

ለኤሌሜንታሪ ፕሮግራሞች፣ ወላጆች በ[ኤሌሜንታሪ የሰመር ት/ቤት ድርጣብያ] ላይ በሚገኘው የምዝገባ ፎርም (mail-in registration form) መገለገል አለባቸው። ፕሮግራሙ በBeall፣ Fields Road እና William Tyler Page ኤሌሜንታሪ ት/ቤቶች ይሰጣል። ክፍለጊዜው የሚጀምረው በጁላይ 8 እና የሚያልቀው በኦገስት 1 ነው። ምዝገባው ጁን 20 ይፈፀማል።

ከኤሌሜንታሪና የ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ተለይቶ ለብቻው ስለሚካሄደው ስለ መካከለኛ ደረጃ ፕሮግራም መረጃ፣ ወላጆች ከልጃቸው ት/ቤት የሰመር ትምህርት አስተባባሪ (Summer School Coordinator) ጋር መገናኘት አለባቸው።

[የ2014 ሰመር ት/ቤት]

**እለቱን ያስታውሱ! የMCPS ልዩ ትምህርት ጠቅላላ ስብሰባ ሜይ 17 እንዲሆን ተወሰነ**

የMCPS ወላጆች፣ ሰራተኞች እና የማህበረሰብ አባላት ለልዩ ትምህርት ጠቅላላ ስብሰባ ተጋብዘዋል፣ *Leading the Way Today, Partnering for a Better Tomorrow (ዛሬ መንገዱን መምራት፣ ለተሻለ ነገ ሽርክና)* ስብሰባው የሚከናወነው ቅዳሜ፣ ሜይ 17፣

ከ8:15 a.m. – 2:30 p.m. በRockville High School, 2100 Baltimore Road in Rockville ነው።

ስብሰባው ቁልፍ ተናጋሪ፣ መገልገያዎች እና ስንኩልና ላላቸው ተማሪዎች ቤተሰቦች ዎርክሾፖች ያስተናግዳል። ወለጆች በተጨማሪ የMCPS ፅ/ቤቶችና የMontgomery County ወኪሎች እና የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን የማግኘት እድል ይኖራቸዋል።

ለስብሰባው ለመመዝገብ፣ [www.mcpsparentacademy.org](http://www.mcpsparentacademy.org)ን ይጎብኙ ወይም 301-517-5940 ይደውሉ። ስብሰባው ነፃ ነው። የህፃናት እንክብካቤ፣ ቀላል ቁርስ፣ እና የምሳ ጥቅሎች ይቀርባሉ።

## የወላጅ አካዴሚ አዳዲስ ዎርክሾፖች ያቀርባል

የMCPS የወላጅ አካዴሚ ለወላጆችና ለማህበረሰብ አባላት የልጆቻቸውን የት/ቤት ስኬት የሚያግዙ መረጃዎች፣ መገልገያዎች፣ መሳርያዎችና ምክሮች የሚሰጡ ዎርክሾፖች ለመከታተል እድል ይሰጣሉ።

የስፕሪንግ የዎርክሾፖች ወራት ሮብ፣ ኤፕረል 2 ይጀምራል። የኮሌጅ መግቢያ ፈተናዎች፣ ውጤታማ የወላጅ ተግባራት፣ የኮምፒውተር ደህንነት (cybersafety) እና የማህበራዊ ሚዲያ፣ እና ሌሎች በርካታ ርእሶች ክፍለ ጊዜዎች አያምልጧችሁ።

[የወላጅ አካዴሚ]()

## ስለ 2ኛደረጃ ት/ቤት እና የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት አማራጮች ተማሩ

በNortheast Consortium (NEC) የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሚኖሩ ወይም የሚከታተሉ የ7ኛ ክፍል ተማሪ ወላጆች ስለ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ኮንሶርሻ (Consortia) አማራጮች፣ የትግባሬ ፕሮግራሞች እና ስለ *Choice* (*ምርጫ*) ሂደት የመረጃ ስብሰባ እንዲያዳምጡ ተጋብዘዋል። ስብሰባው በ7 p.m. ሮብ፣ ኤፕረል 23፣ Springbrook High School, 201 Valleybrook Drive in Silver Spring ይከናወናል።

በDowncounty Consortium (DCC) የሚገኙ የ7ኛ ክፍል ተማሪ ወላጆች ተመሳሳይ የመረጃ ስብሰባ እንዲያዳምጡ ሮብ፣ ኤፕረል 30፣ በWheaton High School, 12601 Dalewood Drive in Silver Spring ተጋብዘዋል።

የ*Choice* ሂደት በተማሪው ስምንተኛ ክፍል አመት በፎል ወራት ይከናወናል። በMiddle School Magnet Consortium (MSMC) ት/ቤት የሚኖሩ ወይም የሚማሩ የ4ኛ ክፍል

ተማሪ ወላጆች በ7 p.m. ሮብ፣ ሜይ 14፣ በRichard Montgomery High School, 250 Richard Montgomery Drive in Rockville በሚከናወን የመረጃ ስባሰባ እንዲከታተሉ ተጋብዘዋል። በስብሰባው ወቅት፣ ወላጆች በተማሪው የአምስተኛ ክፍል አመት የፎል ወራት ተግባራዊ ስለሚሆኑት ስለ ኮንሶርሻ አማራጮች፣ የትግበሬ ፕሮግራሞች እና ስለ *Choice* ሂደት ይማራሉ።

ተጨማሪ መረጃዎች በDivision of Consortia Choice and Application Program Services ድርጣብያ ይገኛሉ።

**ለቦርድ የተማሪ አባል ምርጫ ኤፕረል 30 ይካሄዳል**

የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎቻችሁን በሚመጣው አዲሱ Student Member of the Board of Education (የትምህርት ቦርድ ተማሪ አባል) (SMOB) ምርጫ ሮብ፣ ኤፕረል 30 እንዲያከናውኑ አስታውሷቸው።

ሁለቱ የመጨረሻ ዙር ተወዳዳሪዎች Dahlia Huh (ዳህሊያ ሁህ)፣ በClarksburg High School የ11ኛ ክፍል ተማሪ እና Calvin Yeh (ካልቪን ዬህ) በPoolesville High School የ11ኛ ክፍል ተማሪ ናቸው። ለተጨማሪ መረጃዎችና ፕሮግራሞቻቸውን ለማንበብ የSMOBን ድርጣብያ ጎብኙ።

**Congressman Chris Van Hollen (የፓርላማ አባል ክሪስ ቫን ሆለን)ን በሚመጡት የአገልግሎት አካዴሚ መድረኮች (Service Academy Forums) ይገናኟት።**

ከ9 -11 ክፍሎች የሚገኙ ተማሪዎችና ወላጆቻቸው ስለ ዩ.ኤስ. ያገልግሎት አካዴሚዎችና የመግቢያ ተፈላጊዎች በተጨማሪ ለመማር በCongressman Chris Van Hollen ለሚስታናገዱ መድረኮች ተጋብዘዋል። ከዩ.ኤስ. አየር ሃይል፣ የባህር ጠረፍ ጥበቃ፣ የንግድ ባህረኛ፣ የሚሊታሪና የባህር ሀይል አካዴሚዎች ተወካዮች ማብራርያ ለመስጠትና ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት በቦታው ይገኛሉ። የመጀመርያው መድረክ ሀሙስ፣ ኤፕረል 24፣ ከ7 – 8:30 p.m. በMontgomery County Executive Office Building, 101 Monroe Street ፕሮግራም ተይዞለታል። ሁለተኛው መድረክ ሰኞ፣ ሜይ 5፣ ከ7 – 8:30 p.m. በMcDaniel College, 2 College Hill in Westminster ይካሄዳል።